# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

## የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

### በመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር

### ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ የእርዳታ ቁሳቁሶች አጠባበቅ ስርዓት ላይ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት



ነሐሴ 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ


ክፍል አንድ ........ 1

መግቢያ ........ 1

የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አመሰራረት ........ 1

የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር የተቋቋመበት ዓላማ ........ 2

የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር ........ 2

የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር ስልጣንና ተግባር ........ 3

የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል ........ 4

የገንዘብ ምንጭና አጠቃቀም ........ 4

የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ ........ 4

የክዋኔ የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ........ 4

ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ ........ 5

የኦዲቱ ትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) ........ 5

የኦዲት የመመዘኛ መስፈርት/Audit Evaluative Criteria/ ........ 5

የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር የአሰራር ሂደት መግለጫ ........ 6

የክምችቱ ዓይነትና መጠን ........ 6

የክምችቱ ምንጭ ........ 6

ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችን ወደ መጋዘን ማስገባት ........ 6

የብድር ጥያቄዎች ........ 6

የብድር አሰጣጥ ........ 7

በብድር የወጡትን ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችን ማስመለስ ........ 7

ክፍል ሁለት ........ 8

የኦዲት ግኝት ........ 8

በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች የሚገኙ የምድር ሚዛኖችን በተመለከተ፣ ........ 8

በአስተዳደሩ ቅ/ጽ/ቤት ስር በሚገኙ መጋዘኖች እህል ገቢና ወጪ ሲደረግ የሚመዘን መሆኑን በተመለከተ፣ ........ 9

በመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር ስር ባሉ መጋዘኖች ላይ የሚካሄድ ጥገናን በተመለከተ፣ ........ 10

በአስተዳደሩ ስር በሚገኙ መጋዘኖች ላይ በምግብ ነክ ክምችቶች ላይ የሚካሄዱ የጥራት ፍተሻዎችን በተመለከተ፣ ........ 11

የአስተዳደሩ ማዕከላዊ ላብራቶሪና የምግብ ጥራትና ተባይ ቁጥጥር ቡድን ባለሙያዎች በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚያካሂደው የክምችት ደህንነት ፍተሻን በተመለከተ፣ ........ 12

በአስተዳደሩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ስር ባሉ መጋዘኖች የሚገኘው የእህል ክምችት ተለይቶ ኦዲት የተደረገውና ያልተደረገው ሪፖርት የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ፣ ..... 13
በአስተዳደሩ ስር የሚገኙ መጋዘኖች አጠባበቅን በተመለከተ፣ ..... 14
በአስተዳዳሩ ሥር በሚገኙ መጋዘኖች ያሉ የመጋዘን ሃላፊዎች ስራቸውን የሚያካሂዱባቸው ቢሮዎችን በተመለከተ፣ ..... 15
በአስተዳደሩ ስር በሚገኙ የእህል እና እህል ነክ ያልሆኑ መጋዘኖች የእሳት አደጋ መከላከያ መሣሪያዎች መኖራቸውን በተመለከተ፣ ..... 16
አስተዳደሩ ለተለያዩ ድርጅቶች በብድር የተሰጠውን እህል በተመለከተ፣ ..... 18
የአስተዳዳሩ የመረጃ አያያዝ ስርዓትን በተመለከተ፣ ..... 19
አገልግሎት የማይሰጡት ተንቀሳቃሽ የእህል ሚዛኖችን በተመለከተ፣ ..... 20
በአስተዳደሩ ስር በሚገኙ መጋዘኖች ለአደጋ ጊዜ የሚያገለግሉ የስልክ ቁጥሮች በተገቢው ቦታ መቀመጣቸውን በተመለከተ፣ ..... 21
በአስተዳደሩ ስር በሚገኙ መጋዘኖች የእህል ህክምና ከተደረገ በኋላ ስለሚቀሩ ቁሳቁሶች አወጋገድ በተመለከተ፣ 22
በአስተዳደሩ ስር በሚገኙ መጋዘኖች ለእህል ሕክምና የሚጠቀሙበትን መድኃኒት በተመለከተ፣ ..... 23
በአስተዳደሩ ምግብ ነክ ያልሆኑ ክምችቶች አጠቃላይ ይዞታን በተመለከተ ..... 24
በአስተዳደሩ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ስር በሚገኙ መጋዘኖች አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ጄኔረተሮች መኖራቸውን በተመለከተ፣ ..... 24
ክፍል ሶስት ..... 26
መደምደሚያዎች ..... 26
ክፍል አራት ..... 29
የማሻሻያ ሀሣቦች ..... 29
አባሪ 1 ..... i -- vii

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

## የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አመሰራረት

1. ኢትዮጵያ በተለያየ ጊዜ ካጋጠማት ድርቅና የምግብ እጥረት ችግሮች የተነሳ በምግብ ራሷን ያልቻለች ሀገር እንድትሆን አድርጓታል፡፡ በዝግመትና በድንገት የሚከሰት የምግብ እጥረት ሲኖር የችግሩ ተጠቂ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በቶሎ ለመድረስና ህይወታቸውን ለማዳን እህል በክምችት መልክ መያዝ አስፈላጊ ሆኗል፡፡

2. በዚህም መሰረት የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት በፕሮጀክት መልክ በእርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን ስር በ1974 ዓ.ም ተቋቋመ፡፡ በፕሮጀክት መልክ የተቋቋመው ክምችት፣ እንደ አንድ አደጋን ለመከላከል የሚያስችል የዝግጁነት አቅም በአስተማማኝና ቋሚ በሆነ መልክ እንዲቀጥል ለማድረግ በኢትዮጵያ የሽግግር መንግስት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ጥቅምት 12 ቀን 1987 ዓ.ም በወጣ መመሪያ ተጠሪነቱ ለእርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን የሆነ የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር ተብሎ የሚጠራ መንግስታዊ ተቋም እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

3. በቀጣይነትም አስተዳደሩ የተጣለበትን ኃላፊነት በሚገባ እንዲወጣ ለማድረግና በተጨማሪም ምግብ ነክ ያልሆኑ የእርዳታ ቁሳቁሶች ክምችትንም እንዲይዝ ኃላፊነት በመሠጠቱ ጳጉሜ 1 ቀን 1992 ዓ.ም ከሚኒስትሮች ምክር ቤት በወጣ ደንብ ቁጥር 67/1992 ህጋዊ ሰውነት ተሰጥቶት እንደገና እዲቋቋም ተደርጓል፡፡

4. በመጠባበቂያነት የሚያዘው ዋና የምግብ ክምችት ዓይነት ስንዴ፣ በቆሎ፣ ማሽላና እንደአስፈላጊነቱ ሌሎችንም የሚጨምር ሲሆን ምግብ ነክ ያልሆኑ የእርዳታ ቁሳቁሶች ክምችት ደግሞ የመጠለያ፣ የማብሰያ፣ መመገቢያ፣ የውሀ ማጠራቀሚያ ቁሳቁሶች፣ ፈልጎ ማዳኛ መሳሪያዎችን በእርዳታ ስራ ለሚሰማሩ ሰራተኞች የሚሆኑ መገልገያዎችና ሌሎች መሰል ቁሳቁሶችን የሚያካትት ነው፡፡ የክምችቱ መጠንም የሚወሰነው በቦርዱ ነው፡፡ የምግብ ክምችቱ የሚገኘው በሰባት የተለያዩ ከተሞች ሲሆን እነሱም አዳማ፣ ሻሸመኔ፣ ሺኒሌ፣ ኮምቦልቻ፣ መቀሌ፣ ወላይታ ሶዶ እና ወረታ ናቸው፡፡ የምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ክምችት የሚገኘው አዳማ በሚገኘው መጋዘን ብቻ ነው፡፡ በReview of the strategic role size and structure of the emergency food security Reserve (EFSR)- Phase III ጥናት እንደተገለፀው አስተዳደሩ ባሉት 7 ቅርንጫፎች በሚገኙ መጋዘኖች

የማከማቸት አቅሙ 317000 ሜትሪክ ቶን ሲሆን አስፈላጊ ሲሆን ከሌሎች ድርጅቶች ተጨማሪ መጋዘኖችን በመከራየት እስከ 405,000 ሜትሪክ ቶን እንደሚያከማች ታውቋል፡፡ ከዚህ ውስጥ 70 በመቶ ስንዴ፣ 20 በመቶ በቆሎ እና 10 በመቶ ማሽላ መሆኑ ተገልጿል፡፡ ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች መጠን ደግሞ 10 እንደ አዳራሽ የሚያገለግሉ ድንኳኖች፣ 600 ጥቅል የመጠለያ ፕላስቲክ፣ 20,000 ብርድ ልብሶች፣ 8 የውሀ ማጠራቀሚያዎች፣ 6 የሀይል ማመንጫ ጀነሬተሮች፣ 10,000 አነስተኛ የውሀ ማጠራቀሚያዎች እና 4 የውሀ ማጣሪያ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ የክምችቱ ምንጭ ከእርዳታ ሰጪዎች ከሚገኝ ልገሳ እና ለክምችቱ ማሳደጊያ ከሚደረግ የመንግስት ድጋፍ ነው፡፡

## የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር የተቋቋመበት ዓላማ

አስተዳደሩ የተቋቋመበት ዓላማ የመጠባበቂያ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ክምችት በመያዝ በዝግመትና በፍጥነት የሚከሰቱ አደጋዎች ሲያጋጥሙ ተጨማሪ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ የእርዳታ ቁሳቁሶች ለአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን እና በእርዳታ ስራ ለተሰማሩ ድርጅቶች በብድር መልክ በመስጠት አደጋ ለደረሰበት ህዝብ እንዲከፋፈል ማድረግና በዚህም የአደጋ ሰለባ የሆነው ህብረተሰብ ኑሮ እንዳይናጋና የህይወት መጥፋት እንዳይኖር አስተዋጽኦ ማድረግ ነው፡፡

## የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

5. ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

- ከክምችቱ ጋር የተያያዙ የፖሊሲ ሃሳቦችን የማመንጨት ለመንግሥት የማቅረብና ሲፀድቅም ተግባራዊነታቸውን የመከታተል፣

ክምችቱን ለማሳደግና ደህንነቱን ለመንከባከብ የሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ የመወሰን፣

- ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ የእርዳታ ቁሳቁሶች በብድር ወይም በትውስት እንዲሰጡ የመወሰን፣
- በየጊዜው በብድር ወይም በትውስት የተሰጠው ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ የእርዳታ ቁሳቁሶች በወቅቱ መመለሳቸውን የማረጋገጥ፣
- አስተዳደሩ ከሚኖረው ክምችት ውስጥ በማንኛውም ጊዜ በክምችትነት ሊኖር የሚገባውን አነስተኛ መጠን የመወሰን፣
- በማንኛውም ጊዜ በክምች ሊኖር ከሚገባው አነስተኛ መጠን ላይ በብድር ወይም በትውስት ወጥቶ ሊሰጥ የሚያስፈልግበት ሁኔታ ሲያጋጥም እንዲሰጥ የመወሰን፣
- ከላይ ከተጠቀሱ ሥራዎች ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ መመሪያዎችን ያወጣል፡፡

## የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር ስልጣንና ተግባር

6. የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 67/1992 መሰረት የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር የሚከተለው ስልጣንና ተግባር ተሰጥቶታል፡፡

- ክምችቱን ማስተዳደር፣
- ለክምችት አስፈላጊ የሆነውን ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችን በእርዳታ የማግኘትና የመቀበል እንደአስፈላጊነቱም ከሀገር ውስጥ ወይም ከውጭ ሀገር የመግዛት፣
- በእርዳታ ወይም በግዥ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ የእርዳታ ቁሳቁሶችን የማከማቸት፣
- አስቸኳይ የምግብ እጥረትን ለመቋቋም ይቻል ዘንድ የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት ቦርድ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ከክምችቱ ምግብ በብድር እንዲወጣ የማድረግ፣
- የምግብ ክምችቱን ከተባይ ጥቃት ለመከላከል የሚያስፈልጉ ጸረ-ተባይ ኬሚካሎችንና መድሀኒቶችን የመያዝ በክምችት የቆየ እህልን የማለዋወጥ፣ የምግብ ክምችቱ ላይ የጥራት ቁጥጥር ለማድረግ የሚረዳ ላቦራቶሪ የማደራጀት፣
- ወደ ክምችቱ የሚገባውንና ከክምችቱ የሚወጣውን ምግብ ጥራት የመመርመርና የመቆጣጠር፣ የጥራት ደረጃውን ያልጠበቀ ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ የእርዳታ ቁሳቁሶች ወደ ክምችት እንዳይገቡ የማድረግ፣
- ምግብ ነክ ያልሆኑ የእርዳታ ቁሳቁሶችን የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት ቦርድ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት በብድርና በትውስት መልክ ጥቅም ላይ እንዲውል የማድረግ፣
- መጋዘኖችንና የማከማቻ አገልግሎቶችን የማሰራትና የማከራየት፣
- የንብረት ባለቤት የመሆን፣ ውል የመዋዋል፣ በስሙ የመክሰስና የመከሰስ፣
- የተቋቋመበትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚያግዙ ሌሎች ተመሳሳይ ተግባሮችን የማከናወን

ናቸው፡፡

## የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል

7. በመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር በአዋጅ ቁጥር 67/1992 መሠረት ተጠሪነቱ ለአደጋ መከላከልና ዝግጅት ኮሚሽን የነበረ ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 593/2000 ዓ.ም የኮሚሽኑ ተጠሪነት ለግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር በመተላለፋቸው በአሁኑ ወቅት አስተዳደሩ ተጠሪነቱ ለግብርና ሚኒስቴር ነው፡፡ የመጠባበቂያ ክምችቱን በበላይነት የሚመራና የሚቆጣጠር ቦርድ ተሰይሞለታል፡፡ ለቦርዱ ተጠሪ የሆነ አንድ ስራ አስኪያጅ፣ እና አንድ አማካሪ የቴክኒክ ኮሚቴ ሲኖረው በአምስት መምሪያዎች፣ በሁለት አገልግሎቶች፣ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ጽ/ቤት እና በሰባት የመጋዘን አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የተዋቀረ ነው፡፡

   አስተዳደሩ የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት እንዲችል በመዋቅሩ የተፈቀደለት የስራ መደብ ብዛት 567 ሲሆን በአሁኑ ወቅት በአስተዳደሩ ውስጥ ያለው የሰው ኃይል ብዛት 485 ነው፡፡

## የገንዘብ ምንጭና አጠቃቀም

8. ለመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር ለስራ ማስኬጃ የሚሆን ዓመታዊ በጀት በዋናነት ከመንግስት የሚመደብለት ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ ከሌሎች ምንጮችም ሊገኝ ይችላል፡፡ በመሆኑም ከ2000-2002 ዓ.ም ከመንግሥት የተመደበ በጀት ብር 9,793,500፣ 9,904,000፣ 10,270,700 በቅደም ተከተል ሲሆን ከዚህ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ ብር 9,111,542.22፣ 9,483,065.77፣ 9,247,468.93 በቅደም ተከተል ነው፡፡ የበጀት አጠቃቀሙ በፐርሰንት ሲገለጽ 93%፣ 95.7% እና 90% ነው፡፡

## የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ

9. የኦዲቱ ዓላማ የምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ክምችት አስተዳደር በብቃትና በውጤታማነት እየተከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ ሲሆን ሥራው በብቃትና በውጤታማነት ካልተከናወነ እንዳይከናወን ያደረጉ የአሰራር ድክመቶችን በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚያስችል የማሻሻያ ሃሣብ ለማቅረብ ነው፡፡

## የክዋኔ ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

10. ኦዲቱ የሚሸፍነው ጊዜ ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 2002 ዓ.ም ድረስ ያለውን ጊዜ ነው፡፡
    ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር ሲሆን፣ በአዳማ፣ በሻሸመኔ፣ በወላይታ ሶዶ፣ በሸነሌ፣ በኮምቦልቻ እና በመቀሌ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች እና በስራቸው በሚገኙ መጋዘኖች የኦዲት ቡድኑ በአካል ተገኝቶ መረጃዎችን በመሰብሰብ (Physical

Observation)፣ ዶክሜንቶችን በመከለስ፣ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላዎች ቃለ መጠይቅ በማቅረብ ለኦዲቱ የሚያስፈልጉ ልዩ ልዩ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

## ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ

11.አስተዳደሩ በክምችት የሚይዛቸው ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች በወቅታዊ የፍላጎት ጥናት ላይ የተመሠረቱና ኢኮኖሚያዊና ብቃት ያለው የአጠባበቅና የብድር ሥርዓት ተግባራዊ ስለማድረጉ ማረጋገጥ ነው፡፡

## የኦዲቱ ትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues)

12. ለኦዲቱ ከላይ በተገለፀው የኦዲት አካባቢ ሥር ሦስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ተለይተዋል፡፡ እነርሱም:-

- የአስተዳደሩ የምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ የእርዳታ ቁሳቁሶች ወቅታዊ የፍላጎት ጥናት ክለሳ ስለመደረጉ፣ የክምችቶች ገቢና ወጪ የሥራ አፈጻጸም ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤
- በግዥና በእርዳታ የተገኘ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች አጠባበቅ ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን የተዘረጋውን አሠራር መገመገም፤
- ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ክምችት በብድር የሚሰጥበትና በወቅቱ ተመላሽ እንዲደረግ የሚደረግበትን አሰራር ኢኮኖሚያዊና ውጤታ መሆኑን መገምገም፤

የሚሉት ናቸው፡፡

## የኦዲት የመመዘኛ መስፈርት/Audit Evaluative Criteria/

13. ለተለዩት ሦስት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) 45 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡

14. የኦዲት ቡድኑ የመመዘኛ መስፈርቶቹን ለማዘጋጀት በዋናነት የተጠቀመው የአስተዳደር መ/ቤቱን ተግባርና ኃላፊነት ለመወሰን የወጣን አዋጅ ቁጥር 67/1992፣ በ1987 ዓ.ም የተዘጋጀ Procedure and operational manual እና በ2000 ዓ.ም የተዘጋጀ የክምችትና የብድር መመሪያ ናቸው፡፡

## የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር የአሰራር ሂደት መግለጫ

(Process Description)

## የክምችቱ ዓይነትና መጠን

15. ክምችቱ ምግብ ነክ የሆኑ በዋናነት ስንዴ፣ በቆሎና ማሽላ ምግብ ነክ ካልሆኑት ደግሞ እንደ መጠለያ፣ ማብሰያ፣ መመገቢያ፣ ውሀ ማጠራቀሚያ፣ ፈልጎ ማዳኛ መሳሪያዎችን እና በእርዳታ ለሚሰማሩ ሰራተኞች የሚሆኑ መገልገያዎችን ይያዛል፡፡ በመሆኑም ክምችቱ ሊኖረው የሚገባውን አነስተኛ የክምችት መጠን የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት ቦርድ ይወስናል፡፡

## የክምችቱ ምንጭ

16. ከመንግስት ድጋፍና ከእርዳታ ሰጪዎች በሚገኝ ልገሳ የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር ከሀገር ውስጥ ወይም ከውጭ ሀገር ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችን ይገዛል፡፡

## ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችን ወደ መጋዘን ማስገባት

17. ተገዝተው የመጡት ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች አስፈላጊውን የጥራት መስፈርት ማሟላቱን በምግብ ጥራትና ተባዮች ቁጥጥር ቴክኒሽያኖች አማካይነት ምርመራ ከተደረገላቸው በኋላ በገቢ ማዘዣዎቹ (Receipt Authorization form) አማካይነት ተመዝነው ወደ መጋዘን እንዲገቡ ይደረጋል፡፡ አስተዳደሩ ከቴክኒክ ኮሚቴው በሚያገኘው ምክር መሰረት በእያንዳንዱ ማከማቻ ቦታ የሚቀመጠውን የምግብ ክምችት መጠንና ስብጥር ተግባራዊ በማድረግ ክምችቱን ያደራጃል፡፡

## የብድር ጥያቄዎች

18. የምግብ እጥረት መቋቋሚያ የሚሆኑ የብድር ጥያቄዎች ለአስተዳደሩ ይቀርባሉ፡፡ የቀረቡ የብድር ጥያቄዎች በመጠናቸው ላይ በመመርኮዝ በአስተዳደሩ ዳይሬክተር፣ በአስተዳደሩ የቴክኒክ ኮሚቴ ወይም በቦርዱ አስፈላጊው ምርመራ ከተደረገባቸው በኋላ ውሳኔ ይሰጥባቸዋል፡፡

## የብድር አሰጣጥ

19. ለብድር ጥያቄዎቹ በተሰጠው ውሳኔ መሰረት ብድሩን ለጠየቀው አካል በመመሪያው መሰረትና በወጪ ማዘዣዎቹ (Issue Authorization form) አማካይነት ከመጋዘን ወጪ በማድረግ ብድሩ ይሰጣል፡፡ ብድሩ በሚሰጥበት ጊዜ ከክምችቱ ቀድሞ ከገባው በመውሰድ ተመዝኖ በተጠየቀው መጠን ይሰጣል፡፡

## በብድር የወጡትን ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችን ማስመለስ

20. አስተዳደሩ በብድር የተሰጡ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች በወቅቱ መመለሳቸውን ይከታተላል፡፡ ቦርዱም በአስተዳደሩ አማካኝነት በትውስት የተሰጡ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች በወቅቱ መመለሳቸውን ያረጋግጣል፡፡

# ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝት

### በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች የሚገኙ የምድር ሚዛኖችን በተመለከተ፣

21.የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶቹ ስር በሚገኙ መጋዘኖች የሚገለገልባቸው የምድር ሚዛኖች በትክክል ስለመስራታቸው በመንግስት ኃላፊነት በተሰጠው አካል የብቃት ማረጋገጫ ሰርትፊኬት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ የምድር ሚዛኖቹም በትክክል ስለመሰራታቸው በሚዛን ኦፕሬተሮች ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

22.በኦዲት ወቅት በመስክ ጉብኝት ለማወቅ እንደተቻለው በአስተዳደሩ ስር ከሚገኙት ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች መካከል በሻሸመኔ፣ መቀሌ፣ በኮምቦልቻ እና አዳማ እህል ገቢና ወጪ የሚደረገው በምድር ሚዛን እየተመዘነ ቢሆንም በአሠራር ላይ ግን የሚከተሉት ችግሮች ታይተዋል፡፡

23.የሻሸመኔ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ስራ አስኪያጅ እና የመጋዘን ኃላፊዎች ስለጉዳዩ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ የቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቱ የሚገለገልባቸው ንብረትነታቸው የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት የሆኑ አንድ ማኑዋል እና አንድ ዲጂታል የምድር ሚዛኖች ቢኖሩም ማንዋሉ ከ2002 ዓ.ም ጀምሮ አገልግሎት እንደማይሰጥ ገልፀዋል፡፡ ዲጂታል የምድር ሚዛኑም አልፎ አልፎ ችግር እንደሚገጥመውና የተወሰነ ደረጃ ከመዘነ በኋላም የማተም /Print/ የማድረግ ችግር እንዳለበት ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም ማኑዋሉም ሆነ ዲጂታሉ የምድር ሚዛኖች የመዋዠቅ ችግር ስለሚያጋጥማቸው የመጋዘን ኃላፊዎችን ባለዕዳ እያደረጉ እንደሚገኙ ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም ሚዛኖቹ በትክክል ስለመስራታቸው በራሳቸው ሠራተኞች በየጊዜው ፍተሻና ቁጥጥር የማያደርጉ መሆኑን እና ለዚሁም ዋናው ምክንያት ሚዛኖቹ ንብረትነታቸው የኢትዮጵያ የእህል ንግድ ድርጅት በመሆናቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

24.የአዳማ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ስራ አስኪያጅ ስለጉዳዩ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ እህል ገቢና ወጪ ሲሆን የሚመዘንበት ባለቤትነቱ የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት የሆነ የምድር ሚዛን እንዳለ ገልፀዋል፡፡ ሚዛኑ የቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቱ ባለመሆኑ እና ከቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቱ ግቢ ውጭ በመሆኑ በአሠራር ላይ በመጋዘን ኃላፊዎች ላይ ስጋት እንደፈጠረባቸው ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም ሚዛኑ በትክክል ስለመስራቱ በቅርንጫፍ

ጽሕፈት ቤቱ ሠራተኞች ክትትል ለማድረግ ባለቤትነቱ የሌላ መስሪያ ቤት በመሆኑ እንዳልተቻለ ገልፀዋል፡፡

25.በአስተዳደሩ የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊ ስለጉዳዩ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ የሻሸመኔ እና የአዳማ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች የሚጠቀሙባቸው የምድር ሚዛኖች የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት እንደሆኑና እህል የሚያስመዝኑት በክፍያ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ የምድር ሚዛኖቹ ሲበላሹም ሆነ ችግር ሲያጋጥማቸው ካለብሬት እንዲሆኑ የሚያደርገው ድርጅቱ ራሱ መሆኑን ነገር ግን የአስተዳደሩ የራሱ የምድር ሚዛኖች በሚገኙባቸው በኮምቦልቻና በመቀሌ አስተዳደሩ በራሱ ወጪ እያደረገ በአመት ሁለት ጊዜ ሚዛኖችን ካለብሬት እና ሰርቲፋይ እንደሚያስደርጉ ገልፀዋል፡፡ አስተዳደሩ በሻሸመኔ እና በአዳማ የራሱን የምድር ሚዛን ያልተከተለው ብዙ ወጪ የሚያስወጣና ውድ በመሆኑ ለቁጠባ ታስቦ በኪራይ እየሠሩ እንደሚገኙ ገልፀዋል፡፡

በሻሸመኔ የሚገኘው ማኑዋል የምድር ሚዛን ከ2002 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ማቋረጡ ዲጂታል ሚዛኑም የማተም እና አልፎ አልፎ ችግር የሚያጋጥመው መሆኑ በአዳማ የሚገኘውም የምድር ሚዛን ተመሳሳይ ችግር ያለበት መሆኑ እና በአስተዳደሩ ቴክኒሻኖች ወቅታዊ ክትትል የማይደረግላቸው መሆኑ የቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶቹ ቀልጣፋ አገልግሎት እንዳይሠጡና የመጋዘኖቹ የእህል ገቢና ወጪ ስሌት በትክክል እንዳይታወቅ ሊያደርግና በመጋዘን ሠራተኞቹም ላይ ሚዛኖቹ በሚያሳዩት የስሌት መዋዥቅ ምክንያት የተጠያቂነት ስጋት እንዲፈጠር አድርጓል፡፡

## <u>በአስተዳደሩ ቅ/ጽ/ቤት ስር በሚገኙ መጋዘኖች እህል ገቢና ወጪ ሲደረግ የሚመዘን መሆኑን በተመለከተ፣</u>

26.አስተዳደሩ በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ስር በሚገኙ መጋዘኖች እህል ገቢና ወጪ ሲደረግ መመዘን ይኖርበታል፡፡

27.በአስተዳደሩ ስር ከሚገኙ በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ማለትም ሻሸመኔ፣ ኮምቦልቻ፣ መቀሌ እና አዳማ የምድር ማዛን የሚጠቀሙ ቢሆንም በሽነሌ፣ በወላይታ ሶደና በወረታ የምድር ሚዛን ባለመኖሩ በቆጠራ እህል ገቢና ወጪ እንደሚያደርጉ የኦዲት ቡድኑ በመስክ ባደገው ጉብኝትና ከሥራ ኃላፊዎች ጋር ባደረገው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

28.ይህን አስመልክቶ የአስተዳደሩ የበላይ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት መልስ በሽነሌ በወላይታ ሶዶና በወረታ የመጋዘን ጣቢያዎች የምድር ሚዛን ለማስገባት ቀደም ሲል በነበሩት አመታት የአለም ምግብ ኘሮግራም እርዳታ ተጠይቀው እርዳታው ሊገኝ ባለመቻሉና ባለፈው ዓመት ለሚዛን ግዢ የካፒታል በጀት ጥያቄ ቀርቦ ባለመፈቀዱ በነዚህ ጣቢያዎች ሚዛን አለመኖሩን ገልፀዋል፡፡

29 በነዚህ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች እህል በቆጠራ ገቢና ወጪ መደረጉ ለህገወጥ አሠራር ማለትም ኪሎ የማቀናነስ /ቅሸባ/ እንዲካሄድ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## <u>በመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር ስር ባሉ መጋዘኖች ላይ የሚካሄድ ጥገናን በተመለከተ፤</u>

30.የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር በስሩ የሚገኙ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መጋዘኖች በክምችት የሚይዟቸውን ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች በተገቢው መንገድ ለመጠበቅ እንዲቻል ጥገና ለሚያስፈልገው መጋዘኖች በወቅቱ ጥገና ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

31.በኦዲት ወቅት ከታዩት ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች የሽነሌ፣የኮምቦልቻ እና የአዳማ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ጥገና በወቅቱ የሚካሄድ ሲሆን በወላይታ ሶዶ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ግን የጥገና ባለሙያው ወደ ሌላ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት በመዛወሩ የሚያፈሱ መጋዘኖችን የሚጠግን እንደሌለና በዚህም ምክንያት በክምችት እህል ላይ ጉዳት እየደረሰ መሆኑን እና ችግሩን ለጊዜው ለመፍታት በሚያፈሱ መጋዘኖች ክምችቱን በኘላስቲክ እየሸፈኑ እንደሚገኙ የጽ/ቤቱ የክምችትና ስርጭት ኃላፊ ገልፀዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የመቀሌ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ሰራ አስኪያጅ በኦዲት ቡድኑ ስለጉዳዩ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ ከዚህ በፊት ጥገና በወቅቱ የሚካሄድ እንደነበረና አሁን ግን የጥገና ባለሙያ በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቱ ባለመኖሩ እንዲሁም ባለሙያ ከገበያ ላይ በማጣታቸው የመጋዘን ጥገና ስራን በተመለከተ እንደተቸገሩ ገልፀዋል፡፡

32.በወላይታ ሶዶና በመቀሌ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች የመጋዘን ጥገና ባለሙያዎች ባለመኖራቸው በዝናብ ወቅት የሚያፈሱ መጋዘኖች ጉዳት ከማድረሳቸው በፊት ወቅታዊ ጥገና ስለማይደረግላቸው በክምችት የተያዘውን እህል ለአደጋ ሊያጋልጥ ይችላል፡፡




ፎቶ ግራፍ 1 በወላይታ ሶዶ በጥገና አለመኖር ዝናብ በሚያፈስ መጋዘን የሚገኝ የእህል ክምችት ከዝናብ ለመከላከል በክምችቱ ላይ የተነጠፈ ላስቲክ

## በአስተዳደሩ ስር በሚገኙ መጋዘኖች ላይ በምግብ ነክ ክምችቶች ላይ የሚካሄዱ የጥራት ፍተሻዎችን በተመለከተ፣

33.በአስተዳደሩ ስር የሚገኙ የቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶቹ የእህል ጥራትና ተባይ ቁጥጥር ቴክኒሻኖች በስራቸው በሚገኙ መጋዘኖች ላይ አስተዳደሩ በወጣው መመሪያ መሠረት በወር አንድ ጊዜ ፍተሻ ሊያካሄዱ ይገባል፡፡ በፍተሻው የተገኙ ችግሮችም የጥራት ፍተሻው ለተደረገለት ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት በጽሑፍ መገለጽ ይኖርበታል፡፡

34.የኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች በመገኘት ባካሄደው ኦዲት የእህል ጥራትና ተባይ ቁጥጥር ቴክኒሻኖች በአስተዳደሩ መመሪያ መሠረት ወጥነት ባለው

መልኩ በወር አንድ ጊዜ ፍተሻ የማያከናውኑ ሲሆን ፍተሻው የሚካሄድበት ጊዜ በየቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶቹ የተለያየ መሆኑ ታውቋል፡፡ የኦዲት ቡድኑ በየቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶቹ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ላቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የጥራት ፍተሻው የሚካሄደው እንደአስፈላጊነቱ ተባይ ሊከሰት ይችላል ብለው ባሰቡበት ጊዜ መሆኑን ነገር ግን የግድ ወር እየተጠበቀ የጥራት ፍተሻ እንደማይካሄድ ገልፀዋል፡፡

35.ይህንን አስመልክቶ በአስተዳደሩ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊ በቀረበ ቃለመጠይቅ በሰጡት መልሰ ለወደፊቱ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶቹ የጥራት ፍተሻውን ፎርማቱን ተከትለው ወጥነት ባለው መልኩ እንዲሠሩ እንደሚደረግ ገልፀዋል፡፡

36.በሁሉም ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች የሚገኙ የእህል ጥራትና ተባይ ቁጥጥር ቴክኒሻኖች በአስተዳደሩ መመሪያ መሰረት ወጥነት ባለው መልኩ የጥራት ፍተሻውን በወር አንድ ጊዜ የማያከናውኑ ከሆነ የጥራት ፍተሻው እንዲያስገኝ የሚጠበቀውን ውጤት እንዲያገኝ ሁሉም ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች በሚጠበቀው ደረጃ እየሠሩ መሆኑን ለመከታተል እና ለማረጋገጥ የማያስችል ከመሆኑም በላይ በየቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶቹ ያሉት ድክመቶች ተለይተው የእርምት እርምጃ በወቅቱ እንዳይወሰድባቸውና አሠራራቸውም እንዳይሻሻል ያደርጋል፡፡

## <u>የአስተዳደሩ ማዕከላዊ ላብራቶሪና የምግብ ጥራትና ተባይ ቁጥጥር ቡድን ባለሙያዎች በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚያካሂደው የክምችት ደህንነት ፍተሻን በተመለከተ፣</u>

37. የአስተዳደሩ ማዕከላዊ ላብራቶሪ አገልግሎት እና የምግብ ጥራትና ተባይ ቁጥጥር ቡድን ባለሙያዎች በቅንጅት በየሩብ ዓመቱ በሁሉም የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መጋዘኖች የሚካሂደው የእህል ክምችት ደህንነት የጥራት ፍተሻ ስራው በአግባቡ ስለመካሄዱ የስራ ቁጥጥር ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

38.የኦዲት ቡድኑ በመስክ ተገኝቶ መረጃ በሰበሰበባቸው ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ማለትም በሽንሌ፣ በወላይታ ሶዶ፣ በአዳማ፣ በመቀሌ እና ሻሸመኔ የሚገኙ የእህል ተባይና ጥራት ቁጥጥር ኃላፊዎች እንደገለፁት የአስተዳደሩ ማዕከላዊ ላብራቶሪ አገልግሎት እና የምግብ ጥራትና ተባይ ቁጥጥር ቡድን ባለሙያዎች በቅንጅት በየሩብ ዓመቱ በመገኘት የእህል ክምችት ደህንነት የጥራት ፍተሻ ሥራ በአግባቡ መካሄዱን ካለፉት ሁለት ዓመታት ጀምሮ ያላካሄዱ መሆኑን

39.ይህንን አስመልክቶ በአስተዳደሩ ጉዳይ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ ይህ ስራ ያልተሰራው በመ/ቤቱ ችግር መሆኑን፣ ስራው መቋረጡ በአስራር ላይ ያስከተለው ችግር በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች የጥራትና የተባይ የሱፐርቪዥን ስራ በአግባቡ እንዳይሠራ ማድረጉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም ለችግሩ መከሰት ሌላው ምክንያት የመንግስት የቀን ውሎ አበል ባለመሻሻሉ በቀን 70 ብር እየተከፈለ የሱፐርቪዥን ስራ ለማካሄድ አስቸጋሪ እንዳደረገው ገልፀዋል፡፡

40.የአስተዳደሩ ማዕከላዊ ላብራቶሪ እና የምግብ ጥራትና ተባይ ቁጥጥር የባለሙያዎች ቡድን በቅንጅት በየሩብ ዓመቱ በሁሉም ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች በመገኘት የጥራት ፍተሻ ሥራ በአግባቡ መከናወኑን አለማረጋገጣቸው በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች የሚፈለገው የጥራት ፍተሻ ስራ በአግባቡ እንዳይከናወን ከማድረጉም በላይ በየመጋዘኖቹ የሚያዘው የእህል ክምችት ጥራት የሌለው እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል፡፡

## በአስተዳደሩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ስር ባሉ መጋዘኖች የሚገኘው የእህል ክምችት ተለይቶ ኦዲት የተደረገውና ያልተደረገው ሪፖርት የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ፣

41.በአስተዳደሩ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶቹ ስር በሚገኙ መጋዘኖች የሚገኘው የእህል ክምችት መጠን ኦዲት የተደረገው እና ያልተደረገው ተለይቶ በሪፖርት ማቅረቢያ ቅፅ ላይ ተሞልቶ በየሦስት ወሩ ሪፖርት መደረግ ይኖርበታል፡፡

42.በአስተዳደሩ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ስር በሚገኙ መጋዘኖች የሚገኘው የእህል ክምችት ኦዲት የተደረገው እና ያልተደረገው መጠን ተለይቶ በሪፖርት ማቅረቢያ ቅፅ ላይ ተሞልቶ በየሦስት ወሩ ሪፖርት እንደማይደረግ የኦዲት ቡድኑ በመስክ ስራ በተመለከታቸው ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ማለትም በአዳማ፣ በኮምቦልቻ፣ በሻሸመኔ፣ ወላይታ ሶዶ እና ሸነሌ የሚገኙ የስራ ኃላፊዎች አረጋግጠዋል፡፡

43.ይህንን አስመልክቶ በአስተዳደሩ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልሰ ስራው ያልተሰራው የሰው ኃይል እጥረት በመኖሩ እና አሠራሩ ለዚህ አመቺ ባለመሆኑ ማለትም መዝገቦች እና ቅፆች ለዚህ ስራ የተስተካከሉ ስላልነበረ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም ሪፖርት የሚደረገው በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች በኩል መሆኑን እና አንዳንድ ጊዜ ከሚዘለል በስተቀር እህል ከመጋዘን ወጥቶ ሲያልቅ እህሉ ሙሉ በሙሉ የወጣ

መሆኑ ለክምችት መምሪያ ሪፖርት እየቀረበ በዚህ መሠረት ኦዲት እየተደረገ በየጊዜው ሪፖርት የሚቀርብ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ነገር ግን እህል በመጋዘን እያለ ኦዲት ለማድረግ ከላይ እንደተገለፀው በሰው ኃይል እጥረት እና አሠራሩ ለዚህ ባለመመቻቸቱ አስቸጋሪ እንዳደረገው ገልፀዋል፡፡

44.በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ስር በሚገኙ መጋዘኖች የሚገኘው የእህል ክምችት ኦዲት የተደረገው እና ያልተደረገው መጠን ተለይቶ በሪፖርት ማቅረቢያ ቅፅ ላይ ተሞልቶ በየሦስት ወሩ ሪፖርት አለመደረጉ አስተዳደሩ የክምችቱን መጠን ትክክለኛነት እና በአግባቡም እየተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ የዘረጋው የአሠራር ስርዓት ውጤታማ እንዳይሆን ያደርገዋል፡፡

## <u>በአስተዳደሩ ስር የሚገኙ መጋዘኖች አጠባበቅን በተመለከተ፣</u>

45.አስተዳደሩ በስሩ የሚገኙ የእህል ማከማቻ መጋዘኖች ውስጥ ሌሎች ቁሳቁሶች እንዳይኖሩ እና መጋዘኖቹም በንጽህና እንዲጠበቁ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

46.የኦዲት ቡድኑ በመስክ ስራ በተመለከታቸው ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ማለትም በሻሸመኔ፣ አዳማ፣ ወላይታ ሶዶ፣ ሸነሌ እና ኮምቦልቻ በሚገኙ የእህል መጋዘኖች ውስጥ ሌሎች ቁሳቁሶች ማለትም የተበላሹ ተንቀሳቃሽ ሚዛኖች፣ ወንበሮች፣ የተለያዩ የፅዳት እቃዎች እና ቆርቆሮዎች እንደተቀመጡ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

47.ይህንን በተመለከተ የኦዲት ቡድኑ ለቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶቹ ስራ አስኪያጆች ላቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የተጠቀሱት ቁሳቁሶች በመጋዘኖች ውስጥ መኖር የማይገባቸው ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች እንዳልወጡ፣ ገልጸው ለወደፊቱ ግን ችግሩን ለመፍታት እንዳሰቡ ገልፀዋል፡፡

48.በእህል ማከማቻ መጋዘኖች ውስጥ የተለያዩ ቁሳቁሶች መቀመጣቸው የእህል ገቢና ወጪ በሚኖርበት ወቅት በተፈለገ ሁኔታ ለመንቀሳቀስ የሚያስቸግር ከመሆኑም በላይ ለተባይ መራቢያነት ምቹ ሁኔታን ሊፈጥር ስለሚችል በየመጋዘኖቹ ውስጥ የተከማቸው እህል በተባይ እንዲጠቃ የመጋዘኖቹም ጽዳት በአግባቡ እንዳይካሄድ ሊያደርግ ይችላሉ፡፡



<u>ፎቶግራፍ 2 በናዝሬትቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት</u>
<u>በመጋዘን ውስጥ መቀመጥ የሌለባቸው ቁሳቁሶች የሚያሳይ</u>

## <u>በአስተዳዳሩ ሥር በሚገኙ መጋዘኖች ያሉ የመጋዘን ሃላፊዎች ስራቸውን የሚያካሂዱባቸው ቢሮዎችን በተመለከተ፣</u>

49.በአስተዳደሩ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶቹ መጋዘኖች የሚሰሩ የመጋዘን ሃላፊዎችና ሠራተኞች ሥራቸውን የሚያካሂዱበት ከመጋዘኑ የተለየ ቢሮ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

50.በኦዲት ወቅት በመስክ ስራ መረጃ ከተሰበሰበባቸው የአሰተዳደሩ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ማለትም በአዳማ፣ በሸነሌ፣ በኮምቦልቻ፣ ወላይታ ሶዶ፣ መቀሌ እና ሻሸመኔ በሚገኙ መጋዘኖች የሚሠሩ የመጋዘን ሃላፊዎች እና ሠራተኞች የመጋዘኑን ገቢና ወጪ እንቅስቃሴና ሌሎችንም ስራዎች የሚያካሂዱበት ቢሮ በእህል መጋዘኖች ውስጥ መሆኑን የኦዲት ቡድኑ ተመልክቷል፡፡

51.የቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ሃላፊዎችና የመጋዘን ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የመጋዘን ሃላፊዎቹ ቢሮ መጋዘኖቹ ውሰጥ መሆኑ በመጋዘኑ የተደረደረው እህል ቢናድ በህይወታቸው ላይ ከፍተኛ አደጋ ሊያደርስ እንደሚችልና በእህል ህክምና ወቅትም ሆነ የተለያየ የመድሃኒት ርጭት ከተካሄደ በኋላ የሚፈጠረው የመድሃኒት ሽታም በጤንነታቸው ላይ አደጋ ሊፈጥር እንደሚችል ገልጸዋል፡፡ ለመጋዘን ሃላፊዎች ከመጋዘኖቹ ውጭ የተለየ ቢሮ ለመስራት እስከአሁን የተጀመረ ነገር እንደሌለም አስረድተዋል፡፡

52.በአስተዳደሩ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ስር ባሉ መጋዘኖች ለሚሠሩ የመጋዘን ሃላፊዎች ስራቸውን የሚያካሂዱበት ቢሮ በመጋዘኖቹ ውስጥ መሆኑ የእህል መናድ ቢያጋጥም እንዲሁም ከመድሃኒት ርጭት ጋር በተያያዘ በሚፈጠር ሽታ በሠራተኞቹ ጤንነት ላይ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል። የመጋዘን ኃላፊዎች የስራ ዶክንሜንቶችን ለማስቀመጥ ችግር ይፈጥራል።



ፎቶግራፍ 3 በወላይታ ሶዶ ቅርንጫፍ
የመጋዘን ኃላፊዎች ቢሮ በመጋዘን ውስጥ መሆኑን የሚያሳይ

## <u>በአስተዳደሩ ስር በሚገኙ የእህል እና እህል ነክ ያልሆኑ መጋዘኖች የእሳት አደጋ መከላከያ መሣሪያዎች መኖራቸውን በተመለከተ፣</u>

53.አስተዳደሩ በስሩ በሚገኙ የእህል እና እህል ነክ ያልሆኑ መጋዘኖች በር ላይ በያንዳንዱ መጋዘን ቢያንስ ሁለት የእሳት አደጋ መከላከያ መሣሪዎች ሊኖሩና መሣሪያዎቹም በትክክል

ስለመስራታቸው ወቅታዊ ክትትል ሊደረግ እና መሣሪያዎቹንም በትክክል መጠቀም የሚችሉ ባለሙያዎች ሊሟሉ ይገባል፡፡

54.በኦዲት ወቅት መረጃ በተሰበሰበባቸው የአስተዳደሩ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ማለትም በአዳማ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት በእያንዳንዱ በር ላይ ሁለት የእሳት አደጋ መከላከያ መሣሪያዎች የሚገኝ ቢሆንም በትክክል ስለመሰራታቸው ወቅታዊ ክትትል እንደማይደረግና መሣሪያዎችንም በአግባቡ ሊጠቀሙ የሚችሉ የሠለጠኑ ሠራተኞች እንደሌሉ ታውቋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በኮምቦልቻ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት የእሳት አደጋ መሣሪያዎች ቢኖሩም በየጊዜው ዝግጁ ሆነው እንደማይገኙና የሰለጠነ የሰው ኃይል ባለመኖሩ ለመጠቀም እንደሚቸገሩ ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡ በሻሸመኔ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ውስጥ በሚገኙ መጋዘኖች የእሳት አደጋ መከላከያ መሣሪያዎች ያልተሟሉ ሲሆን ያሉትም መሣሪያዎች በትክክል ስለመሰራታቸው ወቅታዊ ፍተሻ እንደማይደረግላቸውና መሣሪያዎችንም በአግባቡ ለመጠቀም የሚችሉ የሠለጠኑ ሠራተኞች እንደሌሉ ታውቋል፡፡

55.ይህንን አስመልክቶ በአስተዳደሩ ጉዳይ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሣሪያዎች ላይ የታዩት ችግሮች ሊከሰቱ የቻሉት በእውቀት ችግር ማለትም ለዚህ ሥራ የሰለጠኑ ባለሙያዎች ባለመኖራቸው ሲሆን የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሣሪያዎች አንዴ ተሞልተው ካሊብሬት ወይም ክትትል ሳይደረግባቸው እንዲሁ በመቀመጣቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም በዚህ ዓመት በአስተዳደሩም ሆነ በቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች በብዙ ሥራ ተጠምደው የነበረ በመሆኑ እና ጨረታ ቢወጣም ተወዳዳሪ በማጣታቸው ችግሩ ሳይፈታ መቅረቱን ገልጸዋል፡፡ ይሁን እንጂ ከግንቦት 2003 ዓ.ም ጀምሮ ችግሩ ሊፈታ እንደሚችል አስረድተዋል፡፡

56.በአስተዳደሩ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ሥር በሚገኙ መጋዘኖች በቂ የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሣሪያዎች ወቅታዊ ጥገናና ፍተሻ እየተደረገላቸው ተሟልተው ካልተገኙ በመጋዘኖቹ በአጋጣሚ የእሳት አደጋ ቢከሰት በአስተዳደሩ ክምችት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል፡፡



ፎቶግራፍ 4 ኮምቦልቻ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት የተበላሸ የእሳት አደጋ መከላከያ



ፎቶግራፍ 5 በመቀሌ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት
የእሳት አደጋ መከላከያ የሌለው መጋዘን

## አስተዳደሩ ለተለያዩ ድርጅቶች በብድር የተሰጠውን እህል በተመለከተ፣

57. አስተዳደሩ አስቸኳይ የምግብ እጥረትን ለመቋቋም ይቻል ዘንድ የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት ቦርድ በሚያዘው መሠረት ለተለያዩ ድርጅቶች ከክምችቱ በብድር እህል ሊሰጥና የተሰጠውንም ብድር በወቅቱ እንዲመለስ ማድረግ ይጠበቅበታል።

58.በኦዲት ወቅት ከተሰበሰቡ እና ከተከለሱ መረጃዎች ማለትም የቦርድ ቃለጉባዔ እና የክምችትና ስርጭት ወርሃዊ ሪፖርት ላይ እንደተገለፀው ከክምችቱ በብድር የተሰጠ እህል በወቅቱ የማይመለስበት ሁኔታ እንዳለ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተለይ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የዋስትና ደብዳቤ ለግብርና ሚኒስቴር የሴፍቲ ኔት ኘሮግራም ማስፈፀሚያ በብድር የተሰጠ 179,240.65 ሜትሪክ ቶን ቃል በተገባበት ጊዜ በወቅቱ እንዳልተመለስ ታውቋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በአውሮፓ ህብረት ዋስትና ለDRMFSS እንደ ኤሮፓውያን አቆጣጠር በ2006 ዓ.ም በብድር የተሰጠ 24,950.57 ሜትሪክ ቶን እህል ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ እንዳልተመለሰ ታውቋል፡፡

59.ይህንን አስመልክቶ በአስተዳደሩ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ በብድር የሚሰጠው እህል በአብዛኛው በወቅቱ ተመላሽ ይደረጋል ሆኖም በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የዋስትና ደብዳቤ ለግብርና ሚኒስቴር የሴፍቲኔት ኘሮግራም ማስፈፀሚያ የሚሰጥ ብድር አልፎ አልፎ የመዘግየት ሁኔታ ይታይበታል፡፡ ይህም የሚሆነው ግብርና ሚኒስቴር ብድሩን ሲወስድ ከአገር ውስጥ ገዝቶ እንደሚመልስ ታሳቢ በማድረግ ሲሆን ባለፉት አመታት በአገሪቱ ከነበረው የምርት ማነስ የአገር ውስጥ ግዢ ሊፈፀም ባለመቻሉና ከውጪ በመግዛት አስኪመለስ ረጅም ጊዜ በመውሰዱ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

60.አስተዳደሩ ከክምችቱ ለተለያዩ ድርጅቶች በብድር የሚሰጠው እህል በወቅቱ እንዲመለስ ካላደረገ ለሚጠየቅ አደጋም ፈጣን ምላሽ እንዳይሰጥ አስቸኳይ የምግብ እርዳታ ጥያቄ ቢቀርብ በወቅቱ መልስ ለመስጠት በሚደረግ ጥረት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊኖረው ይችላል፡፡

## የአስተዳዳሩ የመረጃ አያያዝ ስርዓትን በተመለከተ፣

61.የመጠባበቂያ የምግብ ክምችት አስተዳደር የውስጥ አሠራሩን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ በተጠናከረ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደራጀ የመረጃ አያያዝ ስርዓት ሊኖረው ይገባል፡፡

62.በኦዲት ወቅት በተካሄደ የመረጃ ክለሳና ቃለመጠይቅ ለማወቅ እንደተቻለው አስተዳደሩ የውስጥ አሠራሩን ቀልጣፋና ውጤታማ ሊያደርግ የሚያስችል በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደራጀ ጠንካራ የመረጃ አያያዝ ስርዓት እንደሌለው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

63.ይህንንም በተመለከተ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የአስተዳደሩ ኃላፊ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ በአስተዳደሩ ስር የሚገኙ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶችን በሠርቨር ለማገናኘት

ስራው ተጀምሮ የነበረ ቢሆንም እስካሁን ግን ውጤታማ አለመሆኑን፣ ለዚህ ስራ የሚያስፈልጉ ሰዎችም ስልጠና ወስደው ተዘጋጅተው የነበረ ቢሆንም ስራው ባለመሳካቱ እንደተቋረጠ፣ በአስተዳደሩ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የመረጃ አያያዝ ስርዓት ለመዘርጋት ታስቦ የነበረ ቢሆንም እስካሁን ተግባራዊ አለመሆኑን፣ ሆኖም ግን በአስተዳደሩ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርዓትን ለማጠናከር እንደታቀደና የትራንስፎርሜሽን እቅዱ ላይም በማካተት ከፍተኛ በጀት እንደተያዘ ገልፀዋል፡፡

64.አስተዳደሩ የውስጥ አሠራሩንና የመረጃ አያያዝ ስርዓቱን በተጠናከረ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አለማደራጀቱ ተቋሙ ቀልጣፋና ውጤታማ ስራን እንዳያከናውን ሊያደርገው ይችላል፡፡

## አገልግሎት የማይሰጡት ተንቀሳቃሽ የእህል ሚዛኖችን በተመለከተ፣

65.አስተዳደሩ ለስራው አስፈላጊ ሆነው በግዥና በእርዳታ ያገኛቸውን የእህል ሚዛኖች በአግባቡ ስራ ላይ ሊያውል፣ ሲበላሹም በወቅቱ ሊያስጠግን እና መጠገን ካልቻሉም የሚወገዱበትን መንገድ ማመቻቸት ይኖርበታል፡፡

66.አስተዳደሩ ከህንድ አገር በእርዳታ ካገኛቸው ከፍተኛ ተንቀሳቃሽ ሚዛኖች መካከል ሰባቱ ሚዛኖች በብልሽት ምክንያት ለረዥም ዓመታት አገልግሎት ሳይሰጡ መቀመጣቸውን የኦዲት ቡድኑ ባካሄደው የመስክ ኦዲት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

67.ይህንን በተመለከተ በአስተዳደሩ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ሚዛኖቹ ለብልሽት ተዳርገው ያለአገልግሎት የተቀመጡበት ምክንያት ወዛደሮች እህሉን ከነጆንያው ያለጥንቃቄ በመጣል ስላበላሿቸው በትክክል እንዳይሠሩ ያደረጓቸው መሆኑን፣ ሚዛኖቹ ያልተጠገኑበት ምክንያትም ቢጠገኑም ሴንሲቲቭ በመሆናቸው መበላሸታቸው የማይቀር በመሆኑና የጥገና ወጪውም እየጨመረ ስለሚሄድ እንዲሁ መተዋቸውን፣ በተጨማሪም እስካሁን እንደምንም ለተወሰነ ጊዜ በጣም ጥቂቶቹ ይሰሩ የነበረ ቢሆንም አሁን ግን አስተዳደሩ ለማስገወድ እቅድ እንደያዘ ገልፀዋል፡፡

68.አስተዳደሩ በእርዳታ ያገኛቸውን የእህል ሚዛኖች በወቅቱ እንዲጠገኑ ወይም መወገድ ካለባቸው እንዲወገዱ ያለማድረጉ ሚዛኖቹ ያለአገልግሎት እንዲቀመጡ እና የሚፈለገውን ውጤት

እንዳያስገኙ ከማድረጉም በላይ መጋዘኖቹንም በማጣበብ በአሠራር ላይ ችግር እንዲፈጥሩ አድርጓል፡፡






ፎቶግራፍ 6 በወላይታ ሶዶ መጋዘን ውስጥ ተበላሽቶ የተገኙ ሚዛኖች

## በአስተዳደሩ ስር በሚገኙ መጋዘኖች ለአደጋ ጊዜ የሚያገለግሉ የስልክ ቁጥሮች በተገቢው ቦታ መቀመጣቸውን በተመለከተ፣

69.በየቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶቹ የሚገኙት የአስተዳደሩ የእህል እና እህል ነክ ያልሆኑ መጋዘኖች በአደጋ ጊዜ እርዳታን ለመጠየቅ የሚያስችሉ የስልክ ቁጥሮች ግልፅ በሆነና በቀላሉ ሊታይ

በሚችል ቦታ ላይ ሊቀመጡ እና ከስራ ሰዓት ውጪ አደጋ ቢከሰት እርዳታ ለመጠየቅ የሚያስችሉ የስልክ አገልግሎቶች ሊሟሉ ይገባል፡፡

70.በኦዲት ወቅት በመስክ ስራ መረጃ ከተሰበሰበባቸው የአስተዳደሩ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ማለትም በኮምቦልቻ፣ በመቀሌ፣ በአዳማ፣ በሻሸመኔ፣ ወላይታ ሶዶ እና ሽነሌ ስር በሚገኙ መጋዘኖች በአደጋ ጊዜ እርዳታ ለመጠየቅ የሚረዱ የስልክ ቁጥሮች ግልጽ በሆነና በቀላሉ ሊታይ በሚችል ቦታ ላይ ያልተቀመጡ እንዲሁም ከስራ ሰዓት ውጪ አደጋ ቢከሰት የተዘጋጀ የስልክ መደወያ ቦታ የሌለ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

71.ይህንን በተመለከተ በአስተዳደሩ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በወቅቱ መጋዘኖቹ ሲገነቡ የአደጋ ጊዜ ማጥሪያ እንዲሆን የታሰበ ነገር ባለመኖሩ መሆኑን ገልፀው አብዛኛዎቹ የቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች መጋዘኖች የተገነቡት ከሁኔታው አስገዳጅነት በአጣዳፊ ሁኔታ በመሆኑ ለአደጋ ጊዜ የሚያገለግሉ የስልክ ቁጥሮች ግምት ውስጥ ሳይገባ መሠራታቸውን እና አሁን ግን ይሄን ለመስራት መዘጋጀታቸውን ገልፀዋል፡፡

72.በቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች በሚገኙ መጋዘኖች በአደጋ ጊዜ አርዳታን ለመጠየቅ የሚያስችሉ የስልክ ቁጥሮች ግልፅ በሆነ ቦታ አለመቀመጣቸው እና ከስራ ሰዓት ውጪ ስልክ መደወያዎች አለመሟላታቸው በመጋዘኖቹ አደጋ ቢከሰት አፋጣኝ እርዳታ እንዳያገኙ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## <u>በአስተዳደሩ ስር በሚገኙ መጋዘኖች የእህል ህክምና ከተደረገ በኂላ ስለሚቀሩ ቁሳቁሶች አወጋገድ በተመለከተ፣</u>

73.በአስተዳደሩ ስር በሚገኙ የእህል መጋዘኖች የእህል ህክምና ከተደረገ በኂላ የሚቀሩ የተለያዩ መድኃኒት የመጣባቸው ቆርቆሮዎችና አመድ በሰውና በአካባቢ ላይ ጉዳት በማያደርስ መልኩ በተገቢው ቦታ ሊቀበሩና ሊወገዱ ይገባል፡፡

74.በኦዲት ወቅት መረጃ በተሰበሰበባቸው ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ማለትም በሽነሌ፡ ኮምቦልቻ፣ መቀሌ፣ ወላይታ ሶዶ፣ አዳማና ሻሸመኔ ከእህል ህክምና በኂላ የሚቀሩት አመድና ቆርቆሮዎች በሰውና በአካባቢ ላይ ጉዳት በማያደርስ መልኩ በተገቢውና ደረጃውን በጠበቀ መልኩ እንደማይወገዱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

75.ይህንን በተመለከተ በአስተዳደሩ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ በተገቢ ሁኔታ እንዲቀበሩ ወይም እንዲወገዱ ስልጠና የተሰጠ ቢሆንም ነገር ግን የተጠናከረ የሱፐርቪዥንና የክትትል ስራ ስለማይደረግ ሁኔታው ሊከሰት እንደቻለ ገልፀዋል፡፡

76.በአስተዳደሩ ስር ባሉ መጋዘኖች የእህል ህክምና ከተደረገ በኋላ የሚቀሩት አመድና ቆርቆሮዎች በተገቢው ሁኔታ እንዲቀበሩ ወይም እንዲወገዱ አለመደረጋቸው በሰዎችና በአካባቢ ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡

## በአስተዳደሩ ስር በሚገኙ መጋዘኖች ለእህል ሕክምና የሚጠቀሙበትን መድኃኒት በተመለከተ፣

77.በአስተዳደሩ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ስር በሚገኙ መጋዘኖች ለእህል ጤንነት መጠበቂያ የሚጠቀሙባቸው መድኃኒቶች ተገቢውን ደረጃ የጠበቁና የመጠቀሚያ ጊዜያቸውም ያላለፈባቸው ሊሆኑ ይገባል፡፡

78.በሸነሌ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ለእህል ህክምና የሚጠቀሙበት መድኃኒት የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈበት መሆኑን የኦዲት ቡድኑ በመስክ ስራ ለማረጋገጥ ችሏል፡፡ ስለጉዳዩ የሸነሌ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ መድኃኒቱ የመጠቀሚያ ጊዜው እንዳለፈበት የሚያውቁ መሆኑን ነገር ግን ዋናው መስሪያ ቤትን ጠይቀው መጠቀም ትችላላችሁ ስለተባለ እንደተጠቀሙበት ገልፀዋል፡፡

79.ይህንን በተመለከተ በአስተዳደሩ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ ምንም እንኳን ጣሳው ላይ የመጠቀሚያ ቀኑ ሁለት ዓመት ቢልም ከጣሳ ውስጥ ካልወጣ የመጠቀሚያ ቀኑ እስከ አራት ዓመት ስለሚቆይ በደብዳቤ ለሸነሌ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት እንዲጠቀሙበት ማዘዛቸውን ገልፀው ከአሁን በኋላ ግን ይህን አይነት አሠራር እንደሚቀር አስረድተዋል፡፡

80.በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ስር የሚኙ መጋዘኖች ለእህል ጤንነት መጠበቂያ የሚጠቀሙባቸው መድኃኒቶች የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው ከሆኑ መድሃኒቶቹ የሚጠበቀውን ውጤት ላያስገኙ ይችላሉ፡፡

## በአስተዳደሩ ምግብ ነክ ያልሆኑ ክምችቶች አጠቃላይ ይዞታን በተመለከተ

81.አስተዳደሩ ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሰቁሶች ለሚፈለጉበት ተግባር በብድርና በትውስት ለመስጠት የሚያስችል ስርዓት በመዘርጋት ክምችቱን በአግባቡ እንዲጠበቅና ለጉዳት እንዳይጋለጥ መጠበቅ ይኖርበታል፡፡

82.አስተዳደሩ በአዳማ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ብቻ ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ማለትም 10 እንደ አዳራሽ የሚያገለግሉ ድንኳኖች፣ 600 ጥቅል የመጠረዣ ኘላስቲክ፣ 20000 ብርድ ልብሶች፣ ባለ 10000 ሊትር 8 የሸራ ውሃ ማጠራቀሚያዎች፣ 6 የሀይል ማመንጫ ጄኔሬተርና የነዳጅ ማጣሪያ፣ ባለ 10 ሊትር 10000 ተጣጣፊ የውሃ ማጠራቀሚያ እና 4 የውሃ ማጣሪያ መሣሪያዎች የሚገኙ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከጥቅም ውጭ የሆኑ 50 ብርድ ልብሶች በክምችት ላይ እያሉ በአይጥ የተበሉና የማያገለግሉ 6 ባለ አስር ሊትር ጀሪካኖች መኖራቸውን የኦዲት ቡድኑ ባካሄደው የመስክ ጉብኝት ለማወቅ ተችሏል፡፡

83.ይህንን አስመልክቶ በአስተዳደሩ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ ክምችቱ ከማነሱ የተነሳ ጠይቆ የሚወስድ ባለመገኘቱ እና ብዙ ጊዜ ያለስራ በመቀመጣቸው ጉዳት እንደደረሰባቸው ገልፀዋል፡፡

84.በአዳማ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች መጋዘን ውስጥ ያለ አገልግሎት ለጉዳት በተጋለጠ ሁኔታ የተከማቹ ቁሳቁሶች መኖራቸው አስቸኳይ የተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ አደጋ ቢከሰት ለተረጂዎች አፋጣኝ መልስ ለመስጠት የሚያስችሉ አገልግሎቶች ላይ መዋል የሚችሉ ቁሳቁሶች እንዳይኖሩ እና ጥያቄውን ለመመለስ አሰቸጋሪ ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል፡፡

## በአስተዳደሩ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ስር በሚገኙ መጋዘኖች አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ጄኔረተሮች መኖራቸውን በተመለከተ፣

85.አስተዳደሩ በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ስር በሚገኙ መጋዘኖች መብራት ሲቋረጥ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ጄኔረተሮች ሊያሟላ ይገባል፡፡

86.በኦዲት ወቅት በመስክ ስራ ከተመለከትናቸው ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ማለትም በሸነሌ፣ በወላይታ ሶዶ፣ በመቀሌ፣ በኮምቦልቻና በሻሸመኔ መብራት ሲቋረጥ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ጄኔሬተር የሌሉ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

87.ይህንን በተመለከተ በአስተዳደሩ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በአዳማ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት አንድ ጄኔሬተር እንዳለና አቅሙ ምን ያህል እንደሆነ እንደማያውቁ፣ በሌሎች ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ግን የካፒታል በጀት ተጠይቆ ስላልተፈቀደ ጄኔሬተር እንደሌላቸውና ወደፊት በሁሉም ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ለማሟላት ሀሳብ መቅረቡን ገልፀዋል፡፡

88.የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር በዝግምትና በድንገት የሚከሰቱ አደጋዎች ሲያጋጥሙ አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የዝግጁነቱ ተቋም በመሆኑ በስሩ የሚገኙ መጋዘኖች ኤሌክትሪክ ሲቋረጥ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ጄኔሬተሮች አለመሟላቱ የምድር ሚዛኖች ስራቸውን እንዲያቋርጡ እና እህል በቆጠራ ገቢና ወጪ እንዲደረግ ስለሚያስገድድ ይህ አሠራሩ የቁጥጥር ስርዓቱን ሊያዛባና ለብልሹ አሠራር በር ሊከፍት እና ተጋላጭ ሊያደርገው ይችላል፡፡

# ክፍል ሶስት

## መደምደሚያዎች

- በሻሸመኔ ቅርንጫፍ የሚገኘው ማኑዋል የምድር ሚዛን ከ2002 ዓም ጀምሮ አገልግሎት ማቋረጡ ዲጂታል ሚዛኑም አልፎ አልፎ ችግር የሚያጋጥመውና የተወሰነ ደረጃ ከመዘነ በኋላ የማተም (print) የማድረግ ችግር ያለበት መሆኑ፣ በአዳማ ቅርንጫፍ ፍሕፈት ቤት የሚኘው የምድር ሚዛን በሌላ ግቢ የሚገኝ መሆኑ፣ የሁለቱም ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች የምድር ሚዛኖቹ ባለቤትነታቸው የኢትዮጵያ የእህል ንግድ ድርጅት በመሆናቸው በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶቹ ባለሙያዎች ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግባቸው መሆኑ፣
- በወላይታ ሶዶ፣ በሽነሌና በወረታ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች እህል ወደ መጋዘን ገቢና ወጪ ሲደረግ በምድር ሚዛን የማይመዘን መሆኑ፣
- በወላይታ ሶዶና የመቀሌ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች የመጋዘን ጥገና ባለሙያዎች ባለመኖራቸው በዝናብ ወቅት የሚያፈሱ መጋዘኖች ጉዳት ከማድረሳቸው በፊት ወቅታዊ ጥገና ለማድረግ አለመቻሉ፣
- በሁሉም ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች የሚገኙ የእህል ጥራትና ተባይ ቁጥጥር ቴክኒሻኖች በአስተዳደሩ መመሪያ መሰረት ወጥነት ባለውና በተመሳሳይ ሁኔታ የጥራት ፍተሻውን በወር አንድ ጊዜ የማያከናውኑ መሆኑ እና የጥራት ፍተሻውም በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ በተለያየ የጊዜ ርቀት መከናወኑ፣
- የአስተዳደሩ ማዕከላዊ ላብራቶሪ እና የምግብ ጥራትና ተባይ ቁጥጥር ባለሙያዎች ቡድን በቅንጅት በየሩብ ዓመቱ በሁሉም ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች በመገኘት የጥራት ፍተሻ ሥራ በአግባቡ መከናወኑን ካለፉት ሁለት ዓመታት ጀምሮ አለመከታተላቸው፣
- በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ስር በሚገኙ መጋዘኖች የሚገኘው የእህል ክምችት ኦዲት የተደረገው እና ያልተደረገው መጠን ተለይቶ በሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ ላይ ተሞልቶ በየሦስት ወሩ ሪፖርት የማይደረግ መሆኑ፣
- በአስተዳደሩ በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ስር ባሉ የእህል መጋዘኖች ውስጥ ሌሎች ቁሳቁሶች መቀመጣቸው፣

- በአስተዳደሩ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ስር ባሉ መጋዘኖች የሚሠሩ የመጋዘን ኃላፊዎች ስራቸውን የሚያካሄዱበት የተለየ ቢሮ የሌላቸው በመሆኑ ሥራቸውን የሚያከናውኑት በመጋዘኖቹ ውስጥ መሆኑ፣

- በአስተዳደሩ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ስር በሚገኙ መጋዘኖች በቂ የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሣሪያዎች አለመሟላታቸው እና ወቅታዊ ጥገናና ፍተሻ የማይደረግላቸው መሆኑ፣

- አስተዳደሩ ከክምችቱ ለተለያዩ ድርጅቶች በብድር የሚሰጠው እህል አልፎ አልፎ በወቅቱ የማይመለስ መሆኑ፣

- አስተዳደሩ የመረጃ አያያዝ ስርዓቱን በተጠናከረ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አለማደራጀቱ፣

- አስተዳደሩ በእርዳታ ያገኛቸው አገልግሎት የማይሰጡ ተንቀሳቃሽ የእህል ሚዛኖች በወቅቱ እንዲጠገኑ ወይም መወገድ የሚገባቸውን እንዲወገዱ አለማድረጉ፣

- በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች በሚገኙ መጋዘኖች በአደጋ ጊዜ እርዳታን ለመጠየቅ የሚያስችሉ የስልክ ቁጥሮች ግልጽ በሆነና በቀላሉ ሊታይ በሚችል ቦታ አለመቀመጥ፣

- በአስተዳደሩ ስር ባሉ መጋዘኖች የእህል ህክምና ከተደረገ በኋላ የሚቀሩት አመድና ቆርቆሮዎች በተገቢው ሁኔታ እንዲቀበሩና እንዲወገዱ አለመደረጉ፣

- በሸነሌ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ለእህል ህክምና የሚጠቀሙበት መድኃኒት የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈበት መሆኑ፣

- በአስተዳደሩ የአዳማ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች መጋዘን ውስጥ ለረዥም ጊዜ ያለአገልግሎት መከማቸታቸው እና በክምችቱም ውስጥ ለጉዳት የተጋለጡ ቁሰቁሶችና መኖራቸው፣

- በአስተዳደሩ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ስር በሚገኙ መጋዘኖች መብራት ሲቋረጥ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ጄኔሬተሮች ያልተሟሉ መሆኑ፣

በኦዲት ወቅት ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህም የሚያሳየው የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር እና በስሩ በሚገኙ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ባሉ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ክምችት አጠባበቅ የጥራት ቁጥጥር እና የብድር ስርዓትን በተመለከተ

የአሠራር ችግር መኖሩን ነው፡፡ በመሆኑም በአስተደደሩ የምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ክምችቶች አጠባበቅና የብድር አሰጣጥ ስርዓት ላይ የታዩትን ክፍተቶች እና የአሠራር ድክመቶች ለማሻሻል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሣቦች በሚቀጥለው የሪፖርት ክፍል አቅርበናል፡፡

## ክፍል አራት

### የማሻሻያ ሀሣቦች

- አስተዳደሩ በሻሸመኔ እና በአዳማ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች የራሱን የምድር ማዛን በማሟላት በራሱ የሚዛን ኦኘሬተሮች ወቅታዊ ክትትል ማድረግ እና በመንግሥት ኃላፊነት በተሰጠው አካል የብቃት ማረጋገጫ እንዲያገኙ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

- አስተዳደሩ በወላይታ ሶዶ፣ በሽነሌ እና በወረታ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች እህል በቆጠራ ገቢና ወጪ የሚካሄድው አሠራር ላይ ሊኖር የሚችለውን ክፍተት ለማሻሻል የምድር ሚዛን እንደሚሟላላቸው ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

- አስተዳደሩ በወላይታ ሶዶና በመቀሌ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች የመጋዘን ጥገና ባለሙያዎችን በማሟላት ወይም በውጪ ባለሞያ በመጠቀም ጥገና የሚያስፈልጋቸው መጋዘኖች በዝናብ ምክንያት በክምችቱ ላይ ጉዳት ከማድረሳቸው በፊት ጥገና ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

- አስተዳደሩ በሁሉም ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች የሚገኙ የእህል ጥራትና ተባይ ቁጥጥር ቴክኒሻኖች ባዘጋጀው መመሪያ መሠረት ወጥነት ባለውና በተመሣሣይ ሁኔታ የጥራት ፍተሻ በወር አንድ ጊዜ እንዲያከናውኑ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

- የአስተዳደሩ ማዕከላዊ ላብራቶሪ እና የምግብ ጥራትና ተባይ ቁጥጥር የባለሙያዎች ቡድን በቅንጅት በየሩብ ዓመቱ በሁሉም ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች በመገኘት የጥራት ፍተሻ ሥራ በአግባቡ መከናወኑን እንዲከታተሉ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

- በአስተዳደሩ ቅ/ጽ/ቤቶች ስር በሚገኙ መጋዘኖች የሚገኘው የእህል ክምችት ኦዲት የተደረገው እና ያልተደረገው መጠን ተለይቶ በሪፖርት ማቅረቢያ ቅፅ ላይ ተሞልቶ በየሦስት ወሩ ሪፖርት መደረግ ይኖርበታል፡፡

- አስተዳደሩ በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ስር በሚገኙ የእህል ማከማቻ መጋዘኖች ውስጥ ሌሎች ቁሳቁሶች እንዳይቀመጡ እና መጋዘኖቹም በንጽሕና እንዲጠበቁ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

- አስተዳደሩ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ስር በሚገኙ መጋዘኖች የሚሠሩ የመጋዘን ኃላፊዎች ቢሮ ከመጋዘኑ ውጭ የተለየ ክፍል እንዲሆን ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

- አስተዳደሩ በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶቹ ስር በሚገኙ መጋዘኖች በቂ የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሣሪያዎች በማሟላት ለመሣሪያዎቹም ወቅታዊ ጥገናና ፍተሻ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

- አስተዳደሩ ከክምችቱ ለተለያዩ ድርጅቶች በብድር የሚሰጠው እህል በወቅቱ እንዲመለስ የሚያስችል የተጠናከረ የክትትል ስራ መስራት ይኖርበታል፡፡

- አስተዳደሩ የመረጃ አያያዝ ስርዓቱን በተጠናከረ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርዓት ሊያደራጅና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- አስተዳደሩ በእርዳታ ያገኛቸውና ያለአገልግሎት የተቀመጡ የእህል ሚዛኖች ተጠግነው ስራ ላይ መዋል የሚችሉት እንዲጠገኑ ሊያደርግ ካልተቻለም እንዲወገዱ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

- አስተዳደሩ በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶቹ ስር በሚገኙ መጋዘኖች በአደጋ ጊዜ እርዳታን ለመጠየቅ የሚያስችሉ የስልክ ቁጥሮች ግልጽ በሆነ ቦታ እንዲቀመጡ ማድረግ እና እንዲሁም ከስራ ሰዓት ውጪ አደጋ ቢከሰት እርዳታ ለመጥራት የሚያሰችል የስልክ አገልግሎት ማሟላት ይጠበቅበታል፡፡

- አስተዳደሩ በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶቹ ስር በሚገኙ መጋዘኖች የእህል ህክምና ከተደረገ በኂላ የሚቀሩት አመድና ቆርቆሮዎች በተገቢው ሁኔታ እንዲቀበሩ ወይም እንዲወገዱ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

- በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ስር የሚገኙ መጋዘኖች ለእህል ጤንነት መጠበቂያ የሚጠቀሙባቸው መድኃኒቶች የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያላለፈባቸው መሆኑን አስተዳደሩ ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡

- አሰተዳደሩ በአዳማ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት የሚገኙትን ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችን በአግባቡ ሊጠብቅና ለጉዳት እንዳይጋለጡ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ለጉዳት የተጋለጡትም በተገቢው መንገድ እንዲወገዱ እና በምትካቸው በቂ ክምችት እንዲያዝ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

- አስተዳደሩ በስሩ በሚገኙ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች መብራት ሲቋረጥ የክምችቱ የገቢና የወጪ ስራ እንዳይስተጓጉል አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ጄኔሬተሮችን ማሟላት ይጠበቅበታል፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት በመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር በዋናው መ/ቤት እንዲሁም በኦዲት ወቅት በተሸፈኑት ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ለተደረገልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

አባሪ 1

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

## (Evaluative criteria)

ኦዲት ተደራጊ መ/ቤት፡- የመጠባቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር

የኦዲት አካባቢ ፡- በግዥ እና በእርዳታ የተገኙ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ክምችቶች የፍላጎት ጥናት ክለሳ ፣ አጠባበቅና በብድር የሚሰጥበትን የስራ ሂደት አፈጻጸም መገምገም፤

| ተ.ቁ. | የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መስፈርቶች (Evaluative Criteria) | የመስፈርቱ ምንጭ (Source of criteria) | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|
| 1. | የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር የምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ የእርዳታ ቁሳቁሶች የፍላጎት ጥናት ክለሳ እና የክምችቶች ገቢ የስራ አፈጻጸምን መገምገም | 1.1. የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት ቦርድ በጥናት በተደገፈ ሁኔታ ክምችቱ ሊይዘው የሚገባውን መጠንና ዓይነት መወሰን አለበት፡፡ | | |
| | | 1.2 የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር የምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ክምችትን በእርዳታ የሚገኘውን በማሰባሰብ እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ ከሀገር ውስጥ ወይም ከውጭ በመግዛት በጥናት የተወሰነውን መጠን ማሟላት አለበት፡፡ | | |
| | | 1.3 የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት ዳይሬክተር የተገዛው ወይም በእርዳታ የተገኘው ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ክምችት ወደ መጋዘን ከመድረሱ በፊት የሚመጣው የምግብ እህል የትኛው መጋዘን መቀመጥ እንዳለበት በመወሰን አስፈላጊው ቅድመ ዝግጅት እንዲደረግ ለክምችትና ስርጭት ክፍል ማሳወቅ አለበት፡፡ | | |
| | | 1.4 የክምችትና ስርጭት ክፍል እህሉ የሚደርስበትን ቀን፣ብዛቱን፣ዓይነቱንና ከየትኛው ወደብ እንደሚመጣ ለመጋዘን ኃላፊው ማሳወቅ አለበት፡፡ | | |
| | | 1.5 ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ወደ መጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር መጋዘን ሲደርሱ ለገቢ ማዘዣነት በተዘጋጀው ፎርም ገቢ | | |

| ተ.ቁ. | የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መስፈርቶች (Evaluative Criteria) | የመስፈርቱ ምንጭ (Source of criteria) | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|
| | | የሚሆንበት ቦታ፣የሚያስገባው ድርጅት ስም፣የእህሉ አይነት፣መጠንና የገቢ ምንጭ እንዲሁም ገቢ እንዲሆን የፈቀደው ባለስልጣን መገለጽ ይኖርበታል፡፡ | | |
| | | 1.6 በመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር በማናቸውም የእህል ገቢ እንቅስቃሴ ወቅት ገቢ እንዲሆን የታዘዘበትን የማዘዣ ቁጥር ተከትሎ ሪፖርት በጥንቃቄ መዘጋጀት አለበት፡፡ | | |
| | | 1.7 ወደ መጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር መጋዘን የሚገቡ እህሎች በሙሉ የመ/ቤቱን የጥራት መስፈርት የሚያሟሉ መሆኑን ለማረጋገጥ የምግብ ጥራትና ተባዮች ቁጥጥር ቴክኒሽያን እህሉ ከመኪና ሳይወርድ ሊደረስበት ከሚቻለው ቦታ ናሙና በመውሰድ የእህሉን የእርጥበት መጠንና የጥራት ደረጃ መመርመር አለበት፡፡ | | |
| | | 1.8 በመመሪያው መሠረት በምርመራ የተረጋገጠው እህል ጥራቱንና የእርጥበት መጠኑ በመላኪያ ሰነድ(Way Bill) ጀርባ ላይ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡ | | |
| | | 1.9 በአስተዳደሩ ስር በሚገኙ የእህል መጋዘኖች ከእህል ህክምና በኂላ የሚቀሩ የተለያዩ ቆርቆሮዎች እና አመድ በሰውና በአካባቢው ላይ ጉዳት በማያደርስ መልኩ በተገቢው ቦታ ሊቀበሩና ሊወገዱ ይገባል፡፡ | | |
| | | 1.10 ክምችቱ ድርድር ለቆጠራ፣ለፍተሻ፣ለህክምና ስራ አመች በሆነ ሁኔታ ማለትም በዓይነት፣በእድሜና በጥራት ደረጃ የተለየ ሆኖ መደርደር ይኖርበታል፡፡ | | |
| | | 1.11 የቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎቹ ዕለታዊ የክምችትና ስርጭት ሪፖርት ወጪ በሚኖርበት ጊዜ፣ገቢ በሚኖርበት ጊዜ፣በእጅ ያለ ክምችት በመጋዘን ውስጥ የሚገኘውን ባዶ ቦታ፣በሚመለከት ሪፖርቱ ለዋናው መ/ቤት መላክ አለባቸው፡፡ | | |
| | | 1.12 በመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር ስር ባሉና የምድር ሚዛን ባለባቸው ጣቢያዎች የምድር ሚዛኖቹ በትክክል ስለመስራታቸው የብቃት ማረጋገጫ በመንግሥት ኃላፊነት ከተሰጠው አካል ሰርተፍኬት | | |

| ተ.ቁ. | የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መስፈርቶች (Evaluative Criteria) | የመስፈርቱ ምንጭ (Source of criteria) | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|
| | | ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ሚዛኖቹ በትክክል መስራት ያለመስራታቸውን በየጊዜው በሚዛን ኦፕሬተሮች ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይገባል፡፡ | | |
| | | 1.13በመጠባበቂያ ምግብ ክምችት የምድር ሚዛን ባለበት መጋዘን ሁሉ እህል ገቢ በሚደረግበት ወቅት መመዘን አለበት፡፡ የምድር ሚዛን ቲኬቱ ተመዝግቦ በሰፈረው መጠን ላይ የሚዛን ሰራተኛውና የመጋዘን ኃላፊው ከፈረሙ በኋላ ቲኬቱ ከገቢ ደረሰኙ ጋር መያያዝ አለበት፡፡ | | |
| 2. | በግዥና በእርዳታ የተገኘ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆነ ክምችት በመጋዘን ውስጥ እያለ ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን የሚደረገውን አጠባበቅ መገምገም | 2.1. በመጠባበቂያ ምግብ ክምችት ስር ያሉ መጋዘኖች የክምችት ቆጠራ በዓመት ሁለት ጊዜ በየስድስት ወሩ የመ/ቤቱ ደንብ በሚፈቅደው መሰረት መከናወን አለበት፡፡ | | |
| | | 2.2. በመጠባበቂያ ምግብ ክምችት ስር ለሚገኙት መጋዘኖች በወር አንድ ጊዜ በየቅ/ጽ/ቤቶቹ ውስጥ ባሉት እህል ጥራትና ቁጥጥር ቴክኒሽኖች አማካኝነት የጥራት ፍተሻ መደረግ አለበት፡፡በጥራት ፍተሻው የተገኙ ግድፈቶችና ችግሮች የጥራት ፍተሻው ለተደረገበት መጋዘን አስ/ቅ/ጽ/ቤት በጽሁፍ መገለጽ አለበት፡፡ | | |
| | | 2.3. በመጠባበቂያ ምግብ ክምችት ለሚገኙ ጥገና የሚያስፈልጋቸው መጋዘኖች በወቅቱ ጥገና መደረግ አለበት፡፡ | | |
| | | 2.4 የዋናው መ/ቤት ማእከላዊ ላብራቶሪ አገልግሎትና የምግብ ጥራትና ተባዮች ቁጥጥር ባለሙያዎች በቅንጅት በየሩብ ዓመቱ በእያንዳንዱ አስ/ቅ/ጽ/ቤት በመገኘት በክምችት ላይ ያለውን የእህል ደህንነት ሁኔታና የጥራት ፍተሻ ስራው በአግባቡ እየተካሄደ ስለመሆኑ የስራ ቁጥጥር ማድረግ አለባቸው፡፡ | | |
| | | 2.5. በመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር ስር ባሉ የመጋዘን ኃላፊዎች ለየክምችት ዓይነቶቹ በሚዘጋጀው ቢን ካርድ ላይ በመጋዘኑ ውስጥ ምን ያህል ክምችት እንዳለው መከታተል አለበት፡፡ | | |

| ተ.ቁ. | የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መስፈርቶች (Evaluative Criteria) | የመስፈርቱ ምንጭ (Source of criteria) | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|
| | | 2.6. በመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር መጋዘን የአንድን ድርድር መጠን፣ ጥራት ቁጥጥርና የህክምና ታሪክ በእስታክ ካርድ ላይ ተመዝግቦ ለመነበብ አመች በሆነ ስፍራ በእያንዳንዱ ድርድር ላይ እንዲንጠለጠል መደረግ አለበት፡፡ መረጃዎቹ በየእለቱ ወቅታዊ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ የድርድሩ ክምችት ወጥቶ ሲያልቅም እስታክ ካርዱ በተገቢ ፋይል ውስጥ ተያይዞ መቀመጥ አለበት፡፡ | | |
| | | 2.7. በየመጋዘኑ ኦዲት የተደረገና ያልተደረገ ክምችት መጠን ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ ላይ ተሞልቶ በየሶስት ወሩ መቅረብ አለበት፡፡ | | |
| | | 2.8. ክምችቱ በተባዮች እንዳይበላና እንዳይበላሽ አስፈላጊውን ህክምናና የተባይ ማጥፊያ መድሀኒት ርጭት መካሄድ አለበት፡፡ | | |
| | | 2.9. በአስተደደሩ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች መጋዘኖች የሚሠሩ የመጋዘን ኃላፊዎች ስራቸውን የሚያካሄዱበት ከመጋዘን በተለየ ቢሮ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ | | |
| | | 2.10 መጋዘኖቹ ውስጥ ከእህሉና ለክምችት ከሚያገለግሉ ቁሳቁሶች ውጪ ሌሎች ቁሳቁሶች እንዳይከማቹ ሊደረግ ይገባል፡፡ | | |
| | | 2.11 መጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር ስር ባሉ የቅ/ጽ/ቤቶች በመዋቅር የተፈቀደ የተመደበና ክፍት የሆነ የስራ መደብ ዝርዝር ተገልጾ በየወሩ ለዋናው መ/ቤት ሪፖርት መቅረብ አለበት፡፡ | | |
| | | 2.12 መጋዘን ጽዳት ፕሮግራም ሊዘጋጅና ግልጽ በሆነና ሊታይ በሚችልበት ስፍራ መቀመጥ አለበት፡፡ | | |
| | | 2.13 ተዘጋጀው የጽዳት ፕሮግራም ተግባራዊ ሊደረግና የመጋዘን ኃላፊውን ጨምሮ የሚመለከታቸው ሰራተኞች በየቀኑ የመጋዘኑንና የክምችቱን ጽዳትና ጠቅላላ ሁኔታ መፈተሽ እንዲሁም መቆጣጠር አለባቸው፡፡ | | |

| ተ.ቁ. | የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መስፈርቶች (Evaluative Criteria) | የመስፈርቱ ምንጭ (Source of criteria) | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|
| | | 2.14መጋዘኖች በር ላይ ቢያንስ ሁለት የእሳት አደጋ መከላከያዎችን ወቅታዊ ክትትል አድርጎ በማሟላት ለእሳት አደጋ መከላከያነት ዝግጁ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡ | | |
| | | 2.15 አስተዳሩ የምግብ ክምችቱን ከፀረ ተባይ ለመከላከል የሚያስችሉ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችና መድሀኒቶችን መያዝ አለበት፡፡ | | |
| | | 2.16በመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር የውስጥ አሠራርን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ የመረጃ አያያዝ ስርዓትን በተጠናከረ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሊያደርግ ይገባል፡፡ | | |
| | | 2.17አስተዳደሩ ለሥራው አስፈላጊ የሆነው በግዥና በእርዳታ ያገኛቸውን ንብረቶች በአግባቡ በስራ ላይ ሊያውል ሲበላሹም ሊያስጠግን እና መጠገን ካልቻሉ የሚወገዱበትን መንገድ ማመቻቸት ይኖርበታል፡፡ | | |
| | | 2.18በየቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች የሚገኙትን የአስተዳደሩ የምግብ እና የምግብ ነክ ያልሆኑ መጋዘኖች በአደጋ ጊዜ እርዳታ ለመጠየቅ የሚያስችሉ የስልክ ቁጥሮች ግልፅ በሆነና በቀላሉ ሊታይ በሚችል ቦታ ላይ ሊቀመጥ ይገባል፡፡ | | |
| | | 2.19በአስተዳደሩ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ስር የሚገኙ መጋዘኖች ለእህል ጤንነት መጠበቂያ የሚጠቀሙባቸው መድኃኒቶች ተገቢውን ደረጃ የጠበቁና የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያላለፈባቸው ሊሆን ይገባል፡፡ | | |
| | | 2.20በአስተዳደሩ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ስር በሚገኙ መጋዘኖች መብራት ሲቋረጥ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ጄኔሬተሮች ሊያሟላ ይገባል፡፡ | | |
| 3. | ምግብና ምግብ ነክ ያልሆነ ክምችት በብድር የሚሰጥበትና በወቅቱ ተመላሽ እንዲደረግ የሚደረግበትን አሰራር መገምገም፡፡ | 3.1. የሚመለከታቸው የአስተዳደሩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሰራተኞች በጋራ በመሆን በክምችት አወጣጥ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገባቸውን ክምችቶች በእድሜና በጥራት ደረጃቸው በመለየት በየጊዜው ሪፖርት ማቅረብ አለባቸው፡፡ | | |

| ተ.ቁ. | የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መስፈርቶች (Evaluative Criteria) | የመስፈርቱ ምንጭ (Source of criteria) | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|
| | | 3.2. ማንኛውም ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ክምችት ወጪ እንዲሆን በሚታዘዝበት ወቅት በወጪ ማዘዣው መሰረት መሆን አለበት፡፡ በመጠባበቂያ ምግብ ክምችት በማናቸውም ክምችት ወጪ እንቅስቃሴ ወቅት ወጪ እንዲሆን የታዘዘበትን የማዘዣ ቁጥር ተከትሎ ሪፖርት በጥንቃቄ መዘጋጀት አለበት፡፡ | | |
| | | 3.3. ማንኛውም በእርዳታ ስራ ላይ የተሰማራ ድርጅት ለአስተዳደሩ የሚያቀርበው የምግብ ብድር ጥያቄ በብድር ጠያቂው ድርጅት የበላይ ኃላፊ ወይም እርሱ በሚወክለው ኃላፊ የተፈረመና መመሪያው የሚጠይቃቸውን ሁኔታዎች ያሟላ መሆን አለበት፡፡ | | |
| | | 3.4. የእርዳታ ሰጪው ድርጅት በሚጠይቀው የብድር መጠን ከታወቀ እርዳታ ሰጪ ድርጅት ወይም በመንግስት ቃል የተገባለት የምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች እርዳታ ያለው ስለመሆኑና በብድር እንዲሰጠው የሚጠይቀውን የብድር መጠን ለመመለስ ቃል ከገባለት የእርዳታ ሰጪ ድርጅት ወይም መንግስት የዋስትና ደብዳቤ ሊኖረው ይገባል፡፡ | | |
| | | 3.5. የምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ብድር ጥያቄ ከመፈቀዱ በፊት በብድር ጠያቂው እጅ ሚገኘውን ቀሪ የክምችት መጠን በቅድሚያ መታወቅ አለበት፡፡ | | |
| | | 3.6. በምርመራ ለሰውም ሆነ ለእንስሳት ለምግብነት ሊውል የማይችል እንደሆነ የተረጋገጠ ምግብ ቦርዱ በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት እንዲቀበር ወይም እንዲቃጠል መደረግ አለበት፡፡ | | |
| | | 3.7. ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች በብድር እንዲወስዱ የተፈቀደላቸው ድርጅቶች በብድር ለሚወስዱት መጠን ውል የመፈረም ግዴታ አለባቸው፡፡የብድሩ ውል በመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር ስራ አስኪያጅና በተበዳሪው ድርጅት የበላይ ኃላፊ ወይም እርሱ በሚወክለው ኃላፊ መካከል መሆን ይኖርበታል፡፡ | | |
| | | 3.8. በብድርና በትውስት የሚሰጡት ምግብ ነክ ያልሆኑ የእርዳታ ቁሳቁሶች ሲመለሱ ተበዳሪው ድርጅት | | |

| ተ.ቁ. | የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መስፈርቶች (Evaluative Criteria) | የመስፈርቱ ምንጭ (Source of criteria) | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|
| | | አይነታቸውና በመስፈርታቸው በተሟላ ሁኔታና ተመልሰው ጥቅም ላይ ሊውሉ በሚችሉበት ሁኔታ መመለስ ይኖርበታል፡፡ | | |
| | | 3.9. የክምችትና ስርጭት መምሪያ በብድር የተሰጠ ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች የመመለሻ ጊዜውን በሚመለከት ሪፖርት ማዘጋጀት አለበት፡፡ | | |
| | | 3.10የብድር መመለሻ ጊዜ ከመድረሱ አንድ ወር ቀደም ብሎ የክምችትና ስርጭት መምሪያ የብድር መመለሻ ጊዜ መድረሱንና አስፈላጊውን ዝግጅት እንዲያደርጉ ለተበዳሪዎች በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡ | | |
| | | 3.11 አስተዳደሩ አስቸኳይ የምግብ እጥረትን ለመቋቋም ይቻል ዘንድ የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት ቦርድ በሚያዘው መሰረት ለተለያዩ ድርጅቶች ከክምችቱ በብድር ሊሰጥና የተሰጠውም ብድር በወቅቱ እንዲመለስ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ | | |
| | | 3.12 አስተዳደሩ ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች በሚፈለጉበት ስፍራ በብድር እና በትውስት ለመስጠት የሚያስችል ስርአት በመዘርጋት ክምችቱን በአግባቡ እንዲጠብቅ እና ለጉዳት እንዳይጋለጥ መጠበቅ ይኖርበታል፡፡ | | |